ጥር 16/2011 ዓ.ም

# የጥሪ ማስታወቂያ

በቅርቡ በአንዳንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተፈጥረው በነበሩ አለመረጋጋቶች ምክንያት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተወሰኑ ግቢዎች ትምህርት ለአጭር ጊዜ ተቋርጦ የነበር ሲሆን በሌሎች ግን ያለምንም ችግር መቀጠሉ ይታወቃል።

አሁን ላይ ሙሉ በሙሉ በዩኒቨርሲቲው ሁሉም ግቢዎች መማር ማስተማሩ በሰላማዊ ሁኔታ እየተካሄደ ይገኛል። ይሁንና በተወሰኑት ግቢዎች ለአጭር ጊዜም ቢሆን ትምህርት ተቋርጦ በነበረበት ወቅት ወጥተው ከነበሩ ከባሕር ዳር ውጪ ያሉ አካባቢዎች ተማሪዎች ውስጥ የተወሰኑት በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳልተገኙ መረጃዎች እያሳዩ በመሆኑ እነዚህ ተማሪዎች እስከ ጥር 22 /2011 ዓ.ም ድረስ ወደግቢያቸው ተመልሰው ሪፖርት በማድረግ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ እናሳስባለን።

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

Bahir Dar University V/President for Information and Strategic Communication